# ትኩረት የሚሹ የህ/ሰብ ክፍሎችና መወሰድ የሚገባቸዉ እርምጃዎች

# 1. ወጣቶች

ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በአብዛኛው የወጣቶች ችግር እየሆነ ነው:: በሌላ በኩል ወረርሽኙን ለማስቆም ከፍተኛ ተስፋ የተጣለውም በወጣቶች ላይ ነው:: ምክንያቱም ወጣቶች ፈጣንና ለቫይረሱ የማያጋልጡ ባህሪያትን ለመፍጠር ከአዋቂዎች የተሻሉ ናቸው:: በየትኛውም አካባቢ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ወረርሽኝ መስፋፋት ፍጥነት ቀንሶ አልያም ተቀልብሶ የታየ ከሆነ ምክንያቱ በዋናነት ወጣት ወንዶችና ሴቶች ራሳቸውን ከቫይረሱ የሚጠብቁባቸው ዘዴዎች/መሳሪያዎችና ማበረታቻዎች ስለተሰጣቸው ነው::

## 1.1 እውነታው

- በኖቬምበር 2003 የታተመ አንድ ፅሁፍ እድሚያቸው ከ15 - 24 የሆነና ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ወጣቶች ቁጥር ወደ 12ሚሊዮን እንደሚጠጋ ይገልፃል::

- በቫይረሱ አዲስ ከሚያዙ ሰዎች መካከል ግማሽ ያህሉ ወጣቶች ናቸው:: በየቀኑ 6ሺህ የሚጠጉ ወጣቶች በኤች.አይ.ቪ ይያዛሉ::

- ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ወጣት ጎረምሶች ወሲብ ይፈፅማሉ:: ስለሆነም ለኤች.አይ.ቪ የተጋለጡ ናቸው::

- ወጣቶች ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ተጋላጭ ከሆኑባቸው መሰረታዊ ምክንያቶች አንዱ ስለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ያለው ዝምታ ነው:: እንዳንድ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በርካታ ወጣቶች ስለኤች.አይ.ቪ ያላቸው ግንዛቤ ዝቅተኛ ወይም የተሳሳተ ነው::

- ሴት ወጣቶች በተለየ ሁኔታ ለኤች.አይ.ቪ ተጋልጠዋል::

- በተለይ ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ አገራት በኤች.አይ.ቪ የሚያዙ ሴት ወጣቶች ቁጥር ከወንድ ወጣቶች በእጥፍ ይበልጣል:: እንደውም በቫይረሱ በጣም በተጠቁ አገራት የሴት ወጣቶች ቁጥር በአምስት ወይም ስድስት እጥፍ በልጦ የሚታይበት ሁኔታ አለ::

- ሴቶች በስነ ህይወታዊ ምክንያት በወሲብ ወቅት በኤች.አይ.ቪ የመያዝ እድላቸው ከወንዶች ይበልጣል:: ብዙውን ጊዜ በእድሜ የገፉ ወንዶች ከወጣት ሴቶች ጋር ወሲብ ስለሚፈፅሙ የሴቶች ተጋላጭነት ይጨምራል::

- የፆታ መድልዎ ባለበት ሴቶች በቂ የትምህርት እድል ስለማይኖራቸው፣ ደካማ ክፍያና የስራ እድል ስለሚገጥማቸው፣ በወንዶች አማካይነት ለጥቃት፣ ህገወጥ ድርጊቶችና ብዝበዛ የተዳረጉ ስለሆነ ላልተፈለገ ወይም ጥንቃቄ ለጎደለው ወሲብ ይጋለጣሉ::

- እንደ አለም አቀፍ የጤና ጥበቃ ድርጅት (WHO) ገለፃ በአባለዘር በሽታዎች ዙሪያ የሚታየው ግድየለሽነት የአለማችን ወጣቶች የጋራ ባህሪ ሆኗል::

በየአመቱ 340 ሚሊዮን ወጣቶች በዓለም ዙሪያ ለአባላዘር በሽታ ይጋለጣሉ:: ይህ አሃዝ በ1990 እ.ኤ.አ ከነበረው መጠን የ40 በመቶ ብልጫ አለው:: ከ340 ሚሊዮን ውስጥ ከግማሽ በላይ እድሜያቸው ከ25 ዓመት በታች በሆኑ ወጣቶች ላይ የደረሰ ሲሆን ከነዚህ ወጣቶች ውስጥ ደግሞ 41በመቶ ያህሉ ጥንቃቄ የጎደለው ወሲብ መፈፀማቸው ሪፖርት ተደርጓል:: (news week,Vol.CXLIV,8,Aug. 23,2004)

- በአገራችን እድሜያቸው ከ10-24 ዓመት የሚሆናቸው ወጣቶች የህዝቡን 32 በመቶ የሚሸፍኑ ሲሆን እድሜያቸው ከ15-24 ዓመት የሆናቸው ከ350-ሺ-620,000 የሚገመቱ ሴቶችና ከ200ሺ-350ሺ የሚገመቱ ወንድ ወጣቶች ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር ይኖራሉ::

- 2001 /እ.ኤ.አ/ የተደረገ ጥናት 19 በመቶ ሴቶችና 3 በመቶ ወንዶች የተቃራኒ ፆታ ወሲብ ከ15 ዓመት እድሜያቸው በፊት መጀመራቸውን ሲያሳይ አማካኝ የወሲብ መጀመሪያ እድሜ ደግሞ ለሴቷ 18 ዓመት ለወንዱ 21 ዓመት ነበር::

- ከአገራችን ነዋሪ 82 በመቶው ስለኤድስ መስማቱን ጥናቶች ቢያረጋግጡም «ጤናማ የሚመስል ሰው ኤች.አይ.ቪ ሊኖርበት ይችላል::» የሚለው እውቀት የነበራቸው 39 በመቶ ሴቶችና 54 በመቶ ወንዶች ብቻ ነበሩ:: «ኮንዶምን በትክክል በመጠቀም 37 በመቶ ሴቶች ብቻ እንደነበሩ እንድ ጥናት ያሳያል::

- ወጣቶች የተስፋ መስኮቶቻችን ናቸው:: በለጋነት እድሜ ውስጥ የሚገኙት ወጣቶች በአብዛኛው ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ አልተጋለጡም /ወሲብ ያልጀመሩ በመሆናቸው /ስለዚህ እነዚህን የህ/ሰብ ክፍሎች ከአደጋው ለመከላከል ከተረባረብን የነገውን የአገርና የህዝብ ተስፋ ብሩህ እናደርጋለን:: ችላ ካልናቸው የሚመጣው አደጋ የከፋ ይሆናል::

- ከዚህ በተጨማሪም ሴቶች በወሲብ ጉዳዮች ዙሪያ በቂ ግንዛቤና ትምህርት መነፈጋቸው ተጋላጭነታቸውን ይጨምራል:: በእርስበርስ ጦርነትና ግጭቶች ወቅትም በአብዛኛው ወጣት ሴቶችና ልጃገረዶች ለወሲብ ጥቃት /አስገድዶ መድፈር/ የተጋለጡ ናቸው:: ግርዛት፣ ያለእድሜ ጋብቻና የውርስ ጋብቻም ሴቶችን ለኤች.አይ.ቪ የበለጠ ተጋላጭ ያደርጋቸዋል::

- አደንዛዥ እፅ የሚጠቀሙ፣ በጦርነት ሳቢያ ለመከራ የተዳረጉ፣ ለወሲብ ብዝበዛ የተዳረጉ፣ ወላጅ አልባ የሆኑ፣ ለጉልበት/የወሲብ ብዝበዛ ከቦታ ቦታ እንዲዘዋወሩ የተገደዱ (Trafficked)፣ ለጎዳና ህይወት የተዳረጉ፣ ወይም በተቋማት የሚኖሩ ወጣቶች ከሌሎቹ እኩዮቻቸው አንፃር የሚያገኙት የመረጃ፣ የክህሎት፣ የአገልግሎት ድጋፍ እድል ዝቅተኛ ነው::

- ወጣቶች የለውጥ ሃይል ናቸው:: ወጣቶችን በማስተባበርና በሰፊው በማንቀሳቀስ በፀረ ኤድስ ትግሉ ማሳተፍ ለጥረታችን ስኬታማነት መሰረት ይሆናል::

## 1.2 ወጣቶችና የአባለዘር በሽታዎች

**ከ1995 - 2003 /እ.ኤ.አ/ በአንዳንድ አገሮች የታየው የአባለዘር በሽታዎች ስርጭት መጠን እድገት /በመቶኛ/**

| Type of STIs | U.S | U.K | Canada | Australia | Russia |
|---|---|---|---|---|---|
| Syphilis | -39% | 1,058% | 47 | -40 | 177 |
| Chlamydia | 69 | 192 | 54 | 360 | - |
| Gonorrhea | 7 | 139 | 40 | 94 | - |
| HIV | -47 | 35 | -60 | -21 | 3,400 |

ምንጭ
Newsweek,
Vol.CXLIV,No.8
Aug.23,2004

ከአባለዘር በሽታዎች ጋር በተያያዘ እየታየ ያለው ችግር በታዳጊ አገሮች ብቻ ሳይሆን በበለፀጉት አገራትም እየተባበሰ ነው:: የፆታና ስነወሲብ ትምህርት በተለይ በታዳጊ አገራት ገና በመጀመር ላይ ሲሆን በተገቢው መጠን እንዳይጠናከር በህ/ሰቡ ውስጥ ያለው የተሳሳተ አመለካከት እንቅፋት ሆኗል::

በቻይና በ1980ዎቹ /እ.ኤ.አ/ መጨረሻ 15 በመቶ የነበረው ቅድመ ጋብቻ ወሲብ አሁን ወደ 70 በመቶ አሻቅቧል:: ሳይንቲስቶች «ድብቁ ወረርሽኝ» እያሉ የሚጠሩት የአባለዘር በሽታ አይነት (Chlamydia) በቻይና አደገኛ ደረጃ ላይ ደርሷል:: በምስራቅ አውሮፖ Syphilis የተባለው የአባለዘር በሽታ ስርጭት ባለፉት 10 ዓመታት በ37 እጥፍ አድጓል::

ወጣቶች እየተሳሳቱ ያሉት የአባለዘር በሽታ በተቃራኒ ፆታ የወሲብ ግንኙነት ወቅት በወሲብ ብልት ዙሪያ ብቻ የሚከሰት /የሚተላለፍ እየመሰላቸው ነው:: እንደ እውነታው ግን የአባለዘር በሽታ በህፃናት /ከእናት ወደ ልጅ/ እንዲሁም በአፍና መሰል የሰውነት ክፍሎች አካባቢም ሊከሰት ይችላል:: በዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ /USA/ ከ1997 /እ.ኤ.አ/ ወዲህ በአፍ አካባቢ የሚከሰት የgonorrhea በሽታ መጠን / እድሜያቸው ከ25 ዓመት በታች በሆኑ ወጣቶች መካካል/ በ60 በመቶ አድጓል::

በአሁኑ ሰዓት ህፃናትና ወጣቶች በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ ያላቸው ብስለትና ብልጠት ከእድሜያቸው በላይ ይመስላል:: ስለዘፋኞች፣ የፊልምና የቲያትር አርቲስቶች፣ ታዋቂ የአለማችን ስፖርተኞች፣ ወዘተ ከአዋቂዎች በላይ ያውቃሉ:: ስለአሜሪካና አውሮፓ ፋሽኖች፣ ስለኢራቅና ፍልስጤም ግጭቶች፣ ስለኮምፒውተርና ሞባይል አጠቃቀም . . . . ብዙ ነገሮች ሊነግሩን ይችላሉ:: ርዕሱን ስለኤድስና ሌሎች የአባለዘር በሽታዎች ጉዳይ ስናዞር ግን እነዚህ ወጣቶች ያላቸው ግንዛቤ አሳዛኝ ሆኖ እናገኘዋለን:: በነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ በተለያዩ ወጣቶች መካከል በርካታ የተሳሳቱ ግንዛቤዎችና አስተሳሰቦች ይንፀባረቃሉ

ወጣቶች ስለአባለዘር በሽታ ትንሽ እውቀት አላቸው ብንል እንኳን ምናልባት ስለChlamydia እና human papilloma virus (HPV, or genital warts) ግን በርካታ ወጣቶች ግንዛቤ የላቸውም:: ስሙንም ሰምተው አያውቁ ይሆናል:: Chlamydia ምልክቶች የማይታይበትና በባክቴሪያ አማካኝነት የሚመጣ ነው:: ህክምና ሳይደረግ ከቆየ መካንነትን ሊያስከትል ይችላል:: በእንግሊዝ ሀገር እድሜያቸው ከ25 ዓመት በታች ከሆኑ ወጣት ሴቶች መካከል 10 በመቶው በዚህ በሽታ እንደተያዙ ይታሰባል:: ስለበሽታው ሰምተው የሚያውቁት ግን በጣም ጥቂቶቹ ብቻ ነበሩ፡ በአሜሪካ 9.1 ሚሊዮን ከ25 ዓመት በታች የሆኑ ወጣቶች በየአመቱ በአባለዘር በሽታ ሲጠቁ ከነዚህ ውስጥ 88 በመቶው በHPV, gonorrhea እና trichomoniasis የተያዙ

ናቸው። በደብሊን /አየርላንድ/ ደግሞ በዚሁ እድሜ ከሚገኑ ወጣቶች 25 በመቶ ያህሉ ለHPV ተጋልጠዋል።

የበሽታዎቹ አደገኛነት ለኤች.አይ.ቪ የመጋለጥ እድልን መጨመር ማስከተሉና ከፍተኛ የጤና ችግር ማምጣታቸው ሲሆን ወጣቶች ግን ምን ማድረግ እንዳለባቸውና እንዴት እንደሚጋለጡ ስለማያውቁ በወቅቱ ህክምና አይሹም።

## 1.3. <u>ወጣቶች ራሳቸውን ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ለመከላከል የሚያስፈልጋቸው</u>

### ሀ. ግንዛቤና መረጃ

- በወሲባዊና ፆታ ጉዳዮች እና በስነ ተዋልዶ ዙሪያ የተሟላ ትምህርት ማግኘትን ይሻሉ።
- ወጣቶች ወሲብ ከመጀመራቸው በፊት በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ በቂ ግንዛቤና ምክር ሊሰጣቸው ይገባል።
- ስለመተላለፊያ መንገዶቹ፣ አደጋውና መከላከያ ዘዴዎች የተሟላ፣ ግልፅና እውነተኛ መረጃ ይፈልጋሉ።
- ከጋብቻ በፊት ከወሲብ መታቀብ ጀምሮ ያሉ ልዩ ልዩ አማራጭ የመከላከያ መንገዶችን መከተል እንዳለባቸው እውቀትና ክህሎት ሊኖራቸው ይገባል።
- ልጃገረዶችን በተለይ ላልተፈለገና ጥንቃቄ ለጎደለው ወሲብ ስለሚያጋልጣቸው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖዎች በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የኤች.አይ.ቪ የምክርና የምርመራ አገልግሎት፣ በመከላከያ ዘዴዎች ዙሪያ በቂ መረጃዎች፣ ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር ለሚኖሩ ወገኖች ድጋፍ፣ እንክብካቤና ህክምና የሚሰጥባቸውን ቦታዎች /ከየት እንደሚገኝ/ መጠቆም
- ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ አንፃር ያላቸውን መብቶችና ያለባቸውን ሃላፊነት በተመለከተም ግንዛቤያቸውን ማሳደግ ጠቃሚ ነው።
- በወጣት ማዕከላት፣ ት/ቤቶች፣ አብያተ እምነቶች፣ በቤተመፅሃፍት፣ በማህበራዊ ተቋማት . . ወዘተ ወጣት ተኮር የመረጃ ስርጭትና አገልግሎት ፣ የመረጃ ማዕከላት፣ የሚኒ ሚዲያና መሰል አገልግሎቶች . . . ወዘተ እንዲዘጋጁላቸው ወጣቶች ይሻሉ።

### ለ. ክህሎትና በራስ የመተማመን ስሜት

- አስቸጋሪ ሁኔታዎችን መሰናክሎችን ማለፍ የሚችሉበት፣ ያልተፈለገ ወይም ጥንቃቄ የጎደለው ወሲብን እምቢ የሚሉበት፣ በባልንጀራ ግፊት አልኮል ወይም አደንዛዥ እፅ መጠቀምን የሚከላከሉበትን ክህሎት ማስጨበጥ። በእርስ በርስ መልካም ግንኙነት፣ ድርድር፣ ግጭትን በሰላማዊ መንገድ ማስወገድ፣ የአድቮኬሲ፣ እቅድ ዝግጅት እና ሌሎች ጠቃሚ ክህሎቶች ያስፈልጓቸዋል።

- ራሳቸውን ከጎጂ ነገሮች ለመከላከል እና ሌሎች ሃላፊነት የሚሰማው ባህሪን ያዳብሩ ዘንድ ወይም ከኤች.አይ.ቪ ራሳቸውን ያርቁ ዘንድ ተፅዕኖ ለማሳደር ብቃት /አቅም/ ሃይል እንዳላቸው የሚያደርግ በራስ የመተማመን ስሜትን ማዳበር።

### ሐ. ወጣት ተኮር አገልግሎቶች

- ፍላጎታቸውን መሰረት ያደረጉ አመቺ ማራኪና በቀላሉ ሊያገኙ የሚችላቸው አገልግሎቶችን ማስፋፋት። ለምሳሌ በጋብቻ ዙሪያ የምክር አገልግሎት፣ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተና ሚስጢራዊ የኤች.አይ.ቪ የምክርና የምርመራ፣

የአባላዘር በሽታዎች ህክምና፣ የመከላከያ ቁሳቁሶች /ኮንዶምን ጨምሮ/ እና የመሳሰሉ አገልግሎቶች ሊስፋፉላቸው ይገባል፡፡

- ጭንቀታቸውን ሃዘናቸውን እና የሚደርስባቸውን መገለል/በተለይ ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ወጣቶች/ መቆጣጠር የሚያስችላቸው የሥነ ልቦና ምክርና ድጋፍ የሚገኙባቸው፡፡

- የአቻ ለአቻ የምክር አገልግሎቶች የሚያገኙባቸው፡፡

መ. ለአደጋ የማያጋልጥ ደጋፊ የሆነ አካባቢ

- ከሚንከባከቧቸው አዋቂዎች /ወላጅ ወይም ሌላ የቤተሰብ አባል ወይም ሞግዚት/ የማያቋርጥ ፍቅርና ድጋፍ፣ የሚያምኑት መምህር፣ የሃይማኖት መሪ ወይም ሃላፊነት የተሰጠው የማ/ሰቡ አባል፡፡

- ወጣቶች በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ፣ በወሲብ ጉዳዮች፣ በሞትና ሌሎች ርዕሶች ዙሪያ የሚሰማቸውን ስሜት የማንም ነቀፌታ ሳይኖር ወይም ሳይፈሩ በነፃና በግልፅ የሚወያዩበት ሁኔታ በእምነት ማ/ሰባቸው ውስጥ እንዲኖር ይሻሉ፡፡

- በማ/ሰባቸው ውሳኔ አሰጣጥ እና ልዩ ልዩ ፕሮግራሞች ውስጥ /በተለይም በወጣቶች ኤች.አይ.ቪ መከላከል ስትራቴጂዎች/ ድምፃቸው እንዲሰማና ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዲኖራቸው ይፈልጋሉ፡፡

- የስራ ፈጣሪነት ክህሎትና እድል የሚያገኙበት አመቺ ሁኔታ እንዲፈጠር ይሻሉ፡፡

- ሃላፊነት ለሚሰማው ባህሪ አርአያ (role model) የሚሆናቸውን ነገር /ሰው/ የሚያገኙበት አካባቢ ሊፈጠርላቸው ይገባል፡፡

## 1.4. <u>ወጣቶችን ለአደጋ የሚያጋልጧቸውን ባህሪያት እንዲቀንሱ የሚረዱ</u>

ሀ. ከአዋቂዎች ጋር አዎንታዊ ግንኙነቶች መኖር፣
ለ. በህ/ሰቡ በቤተሰቡ በሌሎች ቦታዎች ዋጋ እንዳላቸው/ተፈላጊ እንደሆኑ ሲሰማቸው፣
ሐ. ለአደጋ የማያጋልጥና የሚስብ የት/ቤት አካባቢ፣
መ. የመዝናኛ አገልግሎቶች፣
ሠ. አዎንታዊ እሴቶችን፣ ደንቦችንና ከእነርሱ የሚጠበቁ ሁኔታዎችን እንዲያውቁ ሲደረግ፣
ረ. መንፈሳዊ እምነቶች፣
ሰ. በመፃኢው ሁኔታ ብሩህ ተስፋ ሲሰማቸው

## 1.5. ምን መደረግ አለበት?

### ሀ. ዝምታውን መስበር

- ስለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ከወላጆች ጋር መነጋገርና ወላጆች ልጆቻቸውን ከማንኛውም አደጋ ለመጠበቅ የመጀመሪያው ሃይል መሆናቸውን ጠበቅ አድርጎ መንገር:: ወላጆች በወሲብና ፆታዊ ጉዳዮች፣ በአዎንታዊ እሴቶች፣ በግለሰባዊ ሃላፊነት እና ራሳቸውን ከአደጋ ለመከላከል ምን ማድረግ እንዳለባቸው ከልጆቻቸው ጋር እንዲወያዩ ማበረታታትና መርዳት::
- በተለያዩ የወጣት ቡድኖች/ተቋማት ወጣቶች /ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩና በከፍተኛ ሁኔታ ተጋላጭ የሆኑትን ጨምሮ/ እርስ በርሳቸው ስላላቸው ስጋቶችና ተስፋዎች እንዲነጋገሩ በጤናማ ግንኙነትና በመልካም እሴቶች ዙሪያ ግልፅ ውይይት እንዲያደርጉ ማበረታታትና መርዳት::
- ከወጣቶች ጋር የቅርብ ቁርኝት ካላቸው እንደ መምህራን፣ የጤናና የማህበራዊ አገልግሎቶች ሰራተኞች ጋር በቅርብ መወያየት፤

### ለ. ግዴለሽነት ማብቃት

- እንደ የሥርዓተ ፆታ መድልዎ፣ የህፃናት ጥቃት፣ የወሲብ ብዝበዛን አስገድዶ መድፈርና የአደገኛ እፅ መጠቀም ባሉና ወጣቶችን ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ስለሚያጋልጡ ማህበራዊና ባህላዊ ጉዳዮች ውይይት ማድረግ፤

- ወጣቶች «ችግሮች» ሳይሆኑ የችግሮች መፍቻ እንዲሆኑና በራስ አገዝና በበጎ ፍቃድ አገልግሎቶች /በአቻ ለአቻ የምክር አገልግሎቶች፣ በማ/ሰብ ትምህርት፣ በቤት ለቤት እንክብካቤ ወዘተ/ እንዴት አስተዋፅኦ ማበርከት እንደሚችሉ መወያየት፣ ማብራራት፤

### ሐ. ፍራቻንና ጥላቻን መከላከል

- በአካባቢው ያሉ የእምነት ተቋማትና በሰፊው የህ/ሰብ ክፍል ውስጥ የወጣቶችን መንፈሳዊና አካላዊ ፍላጎቶች እንዲረዱ እና ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር ለሚኖሩና ለችግሩ ለተጋለጡ ክፍሎች ተገቢውን ፍቅርና ጥበቃ እንዲያደርጉ ጥሪ ማቅረብ፤

- በማ/ሰብና ተጋላጭ በሆኑ/ከማ/ሰቡ ሥነ ምግባራዊ ፍልስፍና ባፈነገጡ ወጣቶች መካከል ድልድይ በመፍጠር እንዳይገለሉ፣ በተቻለ መጠን እነዚህ ወጣቶች በምክርና ውይይት ወደተፈላጊው ስነምግባር እንዲመጡ፤

- ወጣቶች እየደረሰባቸው ያለው መድሎዎ እንዲወገድ ማድረግ፤

- በድህነት ምክንያት ለአጋላጭ ባህሪያት የተዳረጉና ጥበቃን የሚፈልጉ ወጣቶች ተገቢውን ጥበቃ እንዲያገኙ በመርዳትና አማራጭ የኢኮኖሚ ድጋፍ መንገዶችን በመፍጠር ማገዝ::

### መ. አገልግሎቶችንና ድጋፎችን ማደራጀት

- በሃይማኖት ተቋማት ስር የተደራጁ የወጣቶች ቡድኖችንና ሌሎች የወጣት ጥምረቶችን በመጠቀም ስለኤች.አይ.ቪ. መከላከል ትምህርት ማካሄድ፤

- ኤች.አይ.ቪ.ን የመከላከል ትምህርት በመደበኛና ሰንበት ት/ቤቶች፣ በቤተክርስቲያን ጉባኤዎች፣ በወጣቶች የስብከት፣ የፀሎትና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ፕሮግራሞች፣ በማ/ሰባዊ ማዕከላትና በመሳሰሉት አጋጣሚዎች ሁሉ መስጠቱን ማረጋገጥ፤

- የወጣት ሴቶችን ፍላጎቶች ያገናዘቡና ለወጣቶች አመቺ የሆኑ ወጣት ተኮር የጤናና የማህበራዊ አገልግሎት ተቋማት እንዲቋቋሙና እንዲጠናከሩ ጥረት ማድረግ፣ ማበረታታት /ለምሳሌ ቅድመ ጋብቻ የምክር አገልግሎት፣ ሚስጢራዊና በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የምክርና የኤች.አይ.ቪ. ምርመራ፣ የስነ ተዋልዶ ጤና አጠባበቅ፣ የአደገኛ እፅና አልኮል ጥቃትን የመከላከል፣ የክህሎት ማበልፀጊያና የመረጃ አገልግሎት፣ ለጭንቀትና ሃዘን መፍትሄ የሚሆን ምክር እና መሰል አገልግሎቶችን፤

- የወጣቶች አቻ ለአቻ የመማር፣ የድጋፍና እንክብካቤ ቡድኖችንና ፀረ ኤድስ ክበባት በቤተክርስቲያን ውስጥ ተቋቁመው ባሉ የወጣት ቡድኖች ወይም ለብቻ ራሳቸውን ችለው ለዚህ ተግባር በሚቋቋሙ ቡድኖች ውስጥ ወጣቶች እንዲሳተፉ ማገዝ፤

## ሠ. ማህበራዊ እሴቶችን ማጠናከር

- ወላጆችና ሌሎች አዋቂዎች ልጆቻቸውና ሌሎች ወጣቶች ራሳቸውን ከኤች.አይ.ቪ. ለመከላከል እንዲችሉ የማድረግን ሃላፊነት እንዲቀበሉ ማበረታታት፤ ይህ ደግሞ በወሲባዊ ጉዳዮችና በመከላከል ዙሪያ መሰረታዊ እውቀትን ከማስጨበጥ እንዲሁም ጤናማ ግንኙነትን ከማበረታታትና ወደ መልካም ባህሪይ ለመምራት የሚረዱ አዎንታዊ እሴቶችን ከማስረፅ ይጀምራል/

- ለማህበረ ምዕመኑና ሌሎች ሰዎች ስነ ፆታና ወሲባዊ ጉዳዮች ከማህበራዊ፣ ባህላዊና ሌሎች ይዞታዎች አንፃር ምን እንደሚመስሉና ሌሎችን ከጥቃት የመከላከል አስፈላጊነትን በተመለከተ በሚገባ መንገር /ይህ የልዩ ልዩ ጥቃቶች፣ ግጭቶች፣ ብዝበዛዎች፣ መድልዎችንና የህገወጥ ዝውውር ሰለባ የሆኑ ወጣቶችን ከአደጋ መከላከልን /ማዳንን ሊጨምር ይችላል/

- ሰዎችን ስለኤች.አይ.ቪ.ና መካለከያ መንገዱ የሚያስገነዝቡ ልየ ልዩ ማ/ሰባዊ ፕሮግራሞችን በመቅረፅ እና በማካሄዱ ስራ ወጣቶች ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማበረታታት፣

# 2. ወላጅ አልባ ህፃናት

«ህፃናት በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሳቢያ ለከፋተኛ ጉዳት እየተዳረጉ ነው። ብዙዎች ለህመምና ለጭካኔያዊ ጭቆና ተጋልጠዋል። ማንም ተንከባካቢ የሌላቸው በሚመስል አለም ውስጥ በፍርሃትና በብቸኝነት ተውጠው ይገኛሉ። ከዚህ የባሰ ሽክምም ተጭኖባቸዋል። እነዚህ ህፃናት ለስቃያቸው ምክንያት በሆነው ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሳቢያ ህፍረትና መሸማቀቅ እስኪሰማቸው ድረስ መገለል ደርሶባቸዋል።»

(እ.ኤ.አ በጁን 2002 ኬኒያ ናይሮቢ ላይ በህፃናትና ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ የተሰበሰበው የአፍሪካ የሃይማኖት መሪዎች ጉባኤ ባወጣው የመጨረሻ የጋራ መግለጫ የተወሰደ)

## 2.1 እውነታው

ሀ. በ2003 ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በአለም ላይ 14 ሚሊዮን የሚገመቱ እድሜያቸው ከ15 በታች የሆኑ ህፃናት አንዱን ወይም ሁለቱን ወላጆቻቸውን አሳጥቷቸዋል። ከዚህ ውስጥ 80 በመቶ ያህሉ ከሰሃራ ደቡብ የአፍሪካ አገራት ይገኛሉ እ.ኤ.አ በ2010 ይህ አሃዝ ወደ 25 ሚሊዮን እንደሚደርስ ይገመታል። በሀገራችን የወላጅ አልባ ህፃናት ቁጥር . . . . . . . . . ያህል ሲገመት በክልላችን ደግሞ ወደ 200,000 እንደሚጠጉ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በዚህም ሳቢያ በህፃናት የሚተዳደሩ/የሚመሩ ቤተሰቦች ቁጥር እየጨመረ ነው።

ለ. ኤች.አይ.ቪ በአብዛኛው በግብረስጋ ግንኙነት የሚተላለፍ እንደመሆኑ አንዱን ወላጅ በኤድስ ሳቢያ ያጡ ህፃናት ከጥቂት ጊዜያት በኃላ ሌላኛውንም ወላጅ ያጣሉ።

ሐ. በበርካታ ማ/ሰብ ውስጥ ቤተሰብ ወይም ዘመድ ወላጅ አልባ ህፃናትን ወስደው የመንከባከብ ልማዳዊ ባህል አለ። ሆኖም ግን በኤድስ ሳቢያ የወላጅ አልባ ህፃናት ቁጥር ማ/ሰቡ መሸከም ከሚችለው አቅም በላይ እየጨመረ በመምጣቱ የወላጅ አልባ ህፃናትን ችግር ህ/ሰቡ እንደበፊቱ እንዳይቋቋም አድርጎታል። በተጨማሪም ከዚህ በፊት በአንዳንድ አካላት ይደረግ የነበረው የድጋፍና እንክብካቤ አሰጣጥ ህ/ሰቡ ይህንን መልካም ባህል እንዲረሳው አድርገውታል። የህ/ሰቡን አቅም አምክነውታል።

መ. ህፃናት ቤተሰባቸው ለህመም ሲዳረጉ ወይም ሲሞቱ ከፍተኛ ስቃይ ይደርስባቸዋል። ከሁሉም በላይ ህፃናት እንክብካቤ የሚያደርጉላቸውን አዋቂ የቤተሰብ አባል /ወላጅ/ ሲያጡ ለመቋቋም ለማይችሉትና ለጉዳት ለሚዳርጓቸው የረሃብ፣ ከት/ቤት የማቋረጥ፣ ለአደንዛዥ ዕጽ፣ ለወሲብና ለስነልቦና ጥቃቶች፣ ለጎዳና ህይወት ወዘተ አደጋዎች ይጋለጣሉ። በኤች.አይ.ቪ የመያዝ አደጋም ያጋጥማቸዋል። በክልላችን እ.ኤ.አ. በ2001 ከነበረው ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ውስጥ . . . . ያህሉ ህፃናት ነበሩ።

ሠ. ወላጅ አልባና ሌሎች ተጋላጭ ህፃናት [ሌሎች ተጋላጭ ህፃናት (Other Vulnerable Children) የሚባሉት ወላጆቻቸው ወይም ቤተሰባቸው በኤድስ ሳቢያ ለተደጋጋሚና ረዥም ህመም የተዳረጉባቸውን ህፃናት ነው።] ብዙውን ግዜ የመገለል፣ የመድልዎ፣ የብቸኝነት፣ የቤተሰብ እጦት፣ እና የመሳሰሉ አደጋዎች ተጠቂ ይሆናሉ። ከሚደርስባቸው የኢኮኖሚ ጫና የተነሳም የትምህርትና የጤና አገልግሎት የማግኘት መብታቸውን ይነፍጋሉ። በትምህርት ቤት፣ በቤተ እምነቶችና በማ/ሰባቸው ውስጥ ከፍተኛ የስነልቦና ቀውስ ያጋጥማቸዋል።

ረ. በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በተለየ ምክንያት ወላጅ አልባ የሆኑ ወይም ለአደጋ የተጋለጡ ህፃናትም ከዚህ ላላነሰ ችግር የተዳረጉ ናቸው። እነዚህም በከፍተኛ ደህንነት ውስጥ የሚገኙ፣ ቤት አልባ/የጎዳና ተዳዳሪ፣ በጦርነት ቀጠና ውስጥ የሚኖሩ፣ ለወሲብ ብዝበዛና ለጥቃት የተጋለጡ፣ ከአቅማቸው በላይ የሆኑ አደገኛ ስራ እንዲሰሩ የተገደዱ፣ የታመሙ ወላጆቻቸውን የመንከባከብ ሃላፊነት የተጣለባቸው እና የመሳሰሉ ህፃናት ናቸው። እንደነዚህ ያሉ ህፃናት በበሽታ በቀላሉ ይጠቃሉ፣ ለስነልቦና ቀውስ ይጋለጣሉ፣ ደካማ የአካልና የአዕምሮ እድገት ይኖራቸዋል። በመሆኑም የወላጅ አልባ ህፃናትን ችግሮች ለማቃለል የሚቀረፁ ፕሮግራሞች ሌሎች ተጋላጭ ህፃናትንም ማቀፍ አለባቸው። ይህ ከሞራል አንፃር ተቀባይነት ያለው ተግባር ከመሆኑም በላይ በኤድስ ሳቢያ ወላጅ አልባ የሆኑ ህፃናት ላይ የሚደርስን መገለል ለመከላከል ይረዳል።

## 2.2 <u>ወላጅ አልባና ሌሎች ተጋላጭ ህፃናት ምን ይፈልጋሉ?</u>

### ሀ. ትምህርት

*እንደማንኛውም ህፃን እነዚህ ህፃናትም የትምህርት እድል የማግኘትና ለትምህርት ደጋፊ በሆነና በተደራጀ ምቹ ሁኔታ ውስጥ የማደግ መብት አላቸው።*

### ለ. አገልግሎቶች

*ከትምህርት በተጨማሪ እነዚህ ህፃናት መጠለያና የተመጣጠነ ምግብ፣ የጤና እንክብካቤ፣ የንፁህ ውሃ፣ የንፅህናና መሰረታዊ አገልግሎቶችን ማግኘት አለባቸው። እንደነዚህ ያሉ ህፃናት የህግ ምክርና ድጋፍም ሊያስፈልጋቸው ይችላል። ህፃናቱ እያደጉ ሲሄዱ ደግሞ የራሳቸውን ገቢ ማግኘት የሚችሉበትን ዘዴና ክህሎት ማዳበር አለባቸው።*

### ሐ . የስነ-ልቦና ድጋፍ

*ከታመሙ ወይም በመሞት አፋፍ ላይ ካሉ ወላጆቻቸው ጋር የሚኖሩ ወይም ደግሞ ወላጅ አልባ የሆኑ ህፃናት ብዙውን ጊዜ በዙሪያቸው ካሉ ሌሎች ሰዎች ፍቅር፣ርህራሄና ድጋፍን በእጅጉ ይሻሉ። እንደነዚህ ያሉ ህፃናት ስሜታቸውን ለባለንጀሮቻቸው ወይም የምክር አገልግሎት ሰጪዎቻቸው በተደራጀ ወይም ባልተደራጀ ሁኔታ መገለልና መድልዎ ፍራቻ ሳይኖርባቸው በግልፅ መናገር መቻልም አለባቸው።*

### መ. እንክብካቤ የሚያደርግ ምቹ ሁኔታ /አካባቢ

*ህፃናት ቤተሰቦችና ማ/ሰቦች ሊሰጡ የሚችሏቸውን ግለሰባዊ እንክብካቤዎች፣ ባህላዊ ትስስሮችና የቅርብ ግንኙነቶችን ማግኘት ይሻሉ። የህፃናት /ወላጅ አልባ ህፃናት/ ማሳደጊያ ተቋማት* (Orphanages) *የወላጅ አልባና ሌሎች ተጋላጭ ህፃናትን ቀውስ ለመፍታት ትክክለኛና ዘላቂ መልስ አይደሉም። እንደመጨረሻ አማራጭ ተደርገው መወሰድ አለባቸው። እንደነዚህ ያሉ ተቋማትን ለመምራት የሚጠይቀው ወጪ ለህፃናቱ እንክብካቤ ለሚያደርጉ ቤተሰቦች ድጋፍ ለመስጠት ከሚጠይቀው ወጪ ጋር ሲነፃፀር በጣም ከፍተኛና ውድ ነው።*

በተቻለ መጠን ወላጅ አልባና ሌሎች ተጋላጭ ህፃናት የወደፊት ህይወታቸው ላይ ተፅዕኖ በሚያደርሱ ጉዳዮች ውሳኔ በመስጠት እንዲሳተፉ ማድረግ ይገባል:: ብዙውን ጊዜ እንደነዚህ ያሉ ህፃናት ከእድሜያቸው በላይ ጥበበኛና አርቆ አስተዋይ ናቸው:: በራሳቸውና በሌሎች እህቶቻቸው /ወንድሞቻቸው ጥበቃና እንክብካቤ ዙሪያ ለመወሰን የሚያስችል ብስለት አላቸው::

ጠንካራና ንቁ የማህበራዊ ተቋማት አመራር በወላጅ አልባና ሌሎች ተጋላጭ ህፃናት ላይ የሚደርስ መገለልና መድልዎን ለማቆም ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ:: በማ/ሰቡ ውስጥ በአምልኮ ስፍራዎች ሁሉም ህፃናት እኩል ተቀባይነት ማግኘታቸውን ያረጋግጣል::

## 2.3. <u>ምን ማድረግ ይቻላል</u>

### ሀ. ዝምታውን መስበር

በየጊዜዉ በሚኖረን መርሃ ግብር ወይም የእለት ተእለት አገልግሎት ወይም ሌላ የተለየ ድርጊት ወቅት እንዲሁም ልዩ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ወላጅ አልባ ህፃናትንና እንክብካቤ አድራጊዎቻቸውን ማበረታታት አርአያነታቸዉን ማስተወቅ::

ወላጆቻቸው፣ አሳዳጊዎቻቸው ወይም ተንከባካቢዎቻቸው ለህመም ሲዳረጉ ወይም በሞት ሲለዩዋቸው ህፃናት እንዴት መንፈሳዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ህይወታቸው ሊናጋ እንደሚችል መወያየት::

### ለ. ቸልተኝነትን /ግድየለሽነትን ማብቃት

ማህበረሰቡ በነበረዉ ባህል ከዚህ ቀደም ለወላጅ አልባ ህፃናት እንዴት እንክብካቤና ድጋፍ ያደርጉ እንደነበርና ይህ ሃላፊነት እንዴት የተቀደሰ እንደሆነ መነጋገር/መወያየት:: እያንዳንዱ ወገን በድጋፍና እንክብካቤው ሥራ ቀጥተኛ ተሳታፊ እንዲሆን ማበረታታት::

ወላጅ አልባ ህፃናትና ተንከባካቢዎቻቸው ምን አይነት መንፈሳዊ፣ ስነ ልቡናዊና የስነ ምግባር ምክር፣ ትምህርትና ሌሎች አገልግሎቶችን እንደሚሹ መወያየት፤ ይህ አይነቱን አገልግሎት ሌሎች ህፃናት በከፍተኛ ሁኔታ ሲያስፈልጋቸው እንዴት በአግባቡ ሊሰጣቸው እንደሚችል መነጋገር::

### ሐ. ፍራቻንና ክፋትን /ጥላቻን መከላከል

ወላጅ አልባና ሌሎች ድጋፍና እንክብካቤ የሚሹ ህፃናት ከማ/ሰቡ ተነጥለው በህፃናት ማሳደጊያ ወይም ሌሎች ተቋማት መወርወር እንደሌለባቸውና ማ/ሰብን መሰረት ያደረገ መፍትሄ ላይ ማተኮር እንደሚገባ የሃይማኖት መሪዎችን፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን እና መ/ሰብ አቀፍ ተቋማትን፣ የወጣት ማህበራትን፣ የበጎ አድራጎት ተቋማትን ማሳመን::

እንደነዚህ ያሉ ህፃናት የትምህርት እድልን እንዳያገኙ ያለመደረጉንና /ያለመነፈጋቸውንና/ መድልዎ እየደረሰባቸው ያለመሆኑን ማረጋገጥ። የህፃናት መብቶች ድንጋጌዎችን ለህ/ሰቡ በስፋት ማስተዋወቅ፣ እንዲከበሩ ማበረታታት።

ድጋፍና እንክብካቤ የሚሹ ህፃናት ሁሉ ያለአድልዎ ተገቢውን እውቅናና ትኩረት እንዲያገኙ ጥሪ ማድረግ። በዘርና በጎሳ ወይም በትውልድ/እድገት የማ/ሰቡ አካል ያልሆኑ እና አሳዳጊ/ተንከባካቢ የሚያስፈልጋቸው ህፃናት ላይ መድልዎ እንዳይደርስ መከላከል።

## መ. አገልግሎቶችንና ድጋፍን ማጠናከር/ማደራጀት

በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሳቢያ ጉዳት ለደረሰባቸው ህፃናት የሚሆኑ ልዩ ልዩ አገልግሎቶችን ለማቀናጀትና ለማጠናከር እንዲረዳ ከተለያዩ የማህበረ ሰብና የሃይማኖት ቡድኖች ፣መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ጋር የጋራ ትብብር መድረኮችን መመስረት፤

ወላጅ አልባና ሌሎች ተጋላጭ ህፃናት ለምን የትምህርት ፣ የጤናና ሌሎች መሰረታዊ አገልግሎቶችን ለማግኘት ችግር እንደሚገጥማቸው መለየት። ይህንን ችግር/እንቅፋት ለመቅረፍ የሚያስችሉ ልዩ ልዩ ስልቶችን መቀየስ፤

በርካታ ቁጥር ላላቸው ወላጅ አልባና ሌሎች ተጋላጭ ህፃናት ድጋፍና እንክብካቤ እያደረጉ ላሉ የማ/ሰብ ክፍሎች ድጋፍ ለማድረግ የሚረዱ ዘዴዎችን መፈለግ። ከነዚህ ዘዴዎች ውስጥ ምናልባት የጤናና የትምህርት አገልግሎቶችን የመንፈሳዊና ስነልቦናዊ ድጋፍን፣ የተመጣጠነ ምግብ፣ የንፁህ መጠጥ ውሃና ንፅህና አቅርቦትን ፣ የግብርና ምርታማነትን፣ የራስ አገዝ፣ የገቢ ማስገኛ ስልቶችን ወይም የአነስተኛ ብድርና ቁጠባ . ወዘተ ዘርፎችን መፍጠር ማጠናከርና ማሻሻል ሊገኙበት ይችላል።

በተለያዩ ተቋማት በሚመሩ የትምህርትና የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት የአገልግሎት ክፍያ ቅናሽ በማድረግ አልያም ሙሉ በሙሉ በማስቀረት፤ እንዲሁም ለማ/ሰብ አቀፍ የወላጅ አልባ ህፃናት እንክብካቤና ድጋፍ የሚውል እርዳታን በማሰባሰብ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሳቢያ ለከፋ ችግር ለተጋለጡ ወላጆችን፣ ቤተሰቦችን. . . ወዘተ ድጋፍ በመስጠት ያለባቸውን ኢኮኖሚያዊ ጫና ማቃለል።

በህፃናት ወይም ወላጅ አልባ ህፃናት ለሚመሩ/ ለሚተዳደሩ ቤተሰቦች ድጋፍ ለማድረግ እንቅስቃሴ ሲደረግ ሁል ጊዜ የህፃናቱን ዋና ዋና ፍላጎቶች ማገናዘብ፤ ትኩረት መስጠት። የህፃናቱን የብስለት ደረጃና ችግሮችን የመወጣት ክህሎት/ብቃት ማገናዘብ፣ ወንድምን ወይም እህትን ከመነጠል ይልቅ ቤተሰቡን ተከታታይና ቋሚ የአዋቂ ሰዎች ጉብኝት/ ክትትል በማድረግ መርዳት ፣ ማበረታታት፣ መደገፍ።

እንደወንድም፣ እህት፣ አክስት ወይም አጎት ሆነው ለችግር የተዳረገውን ቤተሰብ የሚንከባከቡ፣ ሌሎች ድጋፍ እንዲያደርጉ የሚያስተባብሩ፣ ለቤተሰቡ የምክርና መንፈሳዊ ድጋፍ፣የህይወት ክህሎት፣ የኑሮ አመራር ወዘተ የሚሰጡ በጎ ፈቃደኞችን ማስተባበርና ማሰማራት።

## ሠ. ማህበራዊ እሴቶችንና ፖሊሲዎችን ማጠናከር

የወላጅ አልባ ህፃናትንና የትዳር ጓደኛቸውን በሞት የተለዩዋቸው ሴቶችን የንብረትና የተወላጅነት፣ እንዲሁም ሌሎች ሰብአዊ መብቶች ማስከበር፤

ወላጅ አልባና ሌሎች ተጋላጭ ህፃናት ከሌሎች እኩዮቻቸው ጋር እኩል የሆነ የመጠለያ፣ የትምህርት፣ የአምልኮ፣ የምክርና ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶች ተጠቃሚ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤

ወላጅ አልባና ሌሎች ተጋላጭ ህፃናትን ከየትኛውም አይነት ጥቃት፣ የመብት ረገጣና ብዝበዛ መጠበቅ፤

ቤተሰብንና ማ/ሰብን መሰረት ያደረገ ድጋፍና እንክብካቤን ማጠናከር ማበረታታት። ከዘመዶቻቸው/ቤተሰቦቻቸው ተነጥለው በተቋማት እንዲኖሩ የተደረጉ ህፃናት ወደማ/ሰባቸው ተመልሰው የሚቀላቀሉበትን መንገድ ማፈላለግ።

# 3. ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ሰዎች

## 3.1 ከኤች.አይ.ቪ ወይም ኤድስ ጋር መኖር

## 3.2 እውነታው

### ሀ. ሁሉም የእምነት ማ/ሰብ ከኤች..አይ.ቪ እና ኤድስ ጋር ይኖራል፡፡

ከኤች.አይ.ቪ ወይም ኤድስ ጋር የሚኖሩ ሰዎች ወንድሞችና እህቶች፣ ልጆች፣ እናቶችና አባቶች ዘመዶች ጓደኞች ናቸው፡፡ የአንዱ ለችግር መዳረግ ብዙዎችን ለችግር ይዳርጋል ወይም የብዙዎች መቸገር ነው፡፡

### ለ. እ.ኤ.አ. በ2002 መጨረሻ በአለማችን 42 ሚሊዮን ያህል ሰዎች ከኤች.አይ.ቪ ወይም ኤድስ ጋር እንደሚኖሩ ተገምቷል፡፡

ከነዚህ ወስጥ 12 ሚሊዮን የሚጠጉት እድሜያቸው ከ15-24 ዓመት የሚሆናቸው ህፃናትና 3.2 ሚሊዮን ደግሞ ከዚያ በታች ያሉ ህፃናት ነበሩ፡፡ እነዚህ ሁሉም ራሳቸው ወይም የሚወዱት ሰው ከገጠመው የከፋ የጤና የመንፈስና ማህበራዊ ፈተናዎች ለማምለጥ ህክምና ድጋፍና እንክብካቤ የሚሹ ናቸው፡፡ በአገራችን ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ዜጎች ቁጥር ከ2.2 ሚሊዮን በላይ እንደሚሆኑና በክልላችን ደግሞ . . . . ያህል እንደሚደርሱ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡

### ሐ. ኤች.አይ.ቪ በደማቸው መኖሩና ያለመኖሩን ማረጋገጥ/ማወቅ ለሰዎች ጠቃሚ ነው፡፡

ሰዎች ኤች.አይ.ቪ በደማቸው ውስጥ እንደሌለ ካረጋገጡ እንዴት ከኤች.አይ.ቪ ራሳቸውን መጠበቅ እንዳለባቸው ያውቃሉ፡፡ ከአጋላጭ ባህሪያት ራሳቸውን ለመለወጥ ይበረታታሉ፡፡ በደማቸው ውስጥ ኤች.አይ.ቪ መኖሩን ያወቁ ሰዎች ደግሞ የባህሪ ለውጥ በማድረግና ተገቢውን የምክር አገልግሎትና ወቅታዊ ህክምና ተጠቃሚ በመሆን ቶሎ ወደ ኤድስ ደረጃ እንዳይደርሱ፣ ራሳቸውን እንዲንከባከቡና እንዲጠብቁ ከስጋትና ጭንቀት እንዲገላገሉ፣ ሌሎችንም ለኤች.አይ.ቪ ከማጋለጥ እንዲቆጠቡ ይረዳቸዋል፡፡

መ. ኤች.አይ.ቪ ወይም ኤድስ መድሃኒት የለውም ግን ረዥም እድሜ ከቫይረሱ ጋር መኖር ይቻላል፡፡

ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖር ሰው በተገቢው ሁኔታ መኖር ከቻለ /Living positively/ ከሌላው ሰው እኩል ጤናማ ህይወት እየመራ ለረዝም አመታት መኖር ይችላል፡፡ በአሁኑ ሰዓት ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ሰዎች ጤናማ ሆነውና ጠንክረው እንዲኖሩ የሚያስችሉ መድሃኒቶች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ "Antiretroviral medicines" /ART/ በመባል ይታወቃሉ፡፡

ሠ. ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ሰዎች ጤናማ ህይወት በተራዘመ ቁጥር ግለሰቡ፣ ቤተሰቡ፣ ማህበረሰቡና አገር በርካታ ጥቅም ይኖራቸዋል፡፡

ህፃናት ወላጅ አልባ አይሆኑም የሚንከባከባቸው ያገኛሉ፡፡ የቤተሰብ ገቢ አይቀንስም ወጪውም አይበዛም፡፡ ቤተሰብና ማ/ሰቡ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሳቢያ ከሚደርስ ተፅዕኖ የሚወጡበትን ስልትና ብልሃት ለመቀየስ ጊዜ ያገኛሉ፡፡ የአምራች ኃይሉ ጉዳት ይቀንሳል፡፡ ማህበራዊ ተቋማት የሰው ሃይል እጥረት አይገጥማቸውም፡፡ ምርታማነት አይጎዳም፡፡ አንድ አገር ለጤና አገልግሎትና ተያያዥ ማህበራዊ ችግሮች የሚያወጣው ወጪ ይቀንሳል፡፡

ረ. ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር ከሚኖሩ ሰዎች ጋር አብሮ መኖር፣ አብሮ መስራትና እንክብካቤ ማድረግ ጉዳት የለውም

ኤች.አይ.ቪ ምግብ አብሮ በመመገብ፣ ብርጭቆ፣ ሰሃን፣ ፎጣ፣ ልብስ፣ መፀዳጃ፣ መቀመጫ፣ ስልክ፣ የቢሮ እቃዎችን፣ ሽንት ቤት፣ ወዘተ በመጋራት ወይም በመጨባበጥ በመሳሳም በመነካካት በማውራት በሳል በለቅሶ ተጠጋግቶ በመቀመጥ እና በመሳሰሉት አይተላለፍም፡፡

ሰ. ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር ለሚኖሩ ሰዎች በቤት ውስጥ እንክብካቤ ማድረግ ይቻላል፡፡

ሁልጊዜ በሳሙና በውሃ በመተጣጠብ የአልባሳትን መኝታንና አካባቢን ንፅህና በመጠበቅ ከኤችአይቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ሰዎችንና እንክብካቤ አድራጊዎችን ከተለመዱት ኢንፌክሽኖች መከላከል ይቻላል፡፡

ሸ. ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ሰዎች ለሚያጋጥማቸው የሳል፣ የተቅማጥ የአፍና የቆዳ ቁስለት፣ እና መሰል በሽታዎች በፍጥነት ህክምና ማግኘት አለባቸው አብዛኛውን ጊዜ አነዚህን ለመሳሰሉ ህመሞች በአካባቢያቸው ከሚገኙ የጤና ኬላዎች፣ ክሊኒኮችና ጤና ጣቢያዎች ተገቢውን ህክምና ሊያገኙ ይችላሉ፡፡

ቀ. Antiretroviral therapy የተሰኘው ህክምና ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር ለሚኖሩ ሰዎች ጤናማ ህይወት ጠቀሜታ አለው፡፡

ይህ መድሃኒት ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ሰዎችን ጤናማ ህይወት የሚያሻሽልና የመኖሪያ እድሜያቸውን የሚያረዝም መሆኑ ቢታወቅም በዋጋው ውድነት፣ መድሃኒቱን ለህይወት ዘመን ሙሉ በቀጣይነት መቀጠል በማስፈለጉ፣ የሰለጠነ የሰው ሃይልና ቴክኖሎጂ በመጠየቁ አጠቃቀሙ ጥንቃቄ የሚጠይቅ በመሆኑ አገሮች ተገቢ የሆነ

ፖሊሲ ቁርጠኛ ድጋፍ ባለማውጣታቸው ሳቢያ በተለይ በታዳጊ አገራት ሰዎች በቀላሉ ሊያገኙት አልቻሉም::

በ. **ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ሰዎች ቤተሰባቸውን ለቀጣዩ ህይወት እንዲያዘጋጁ ምክርና ድጋፍ መደረግ አለበት::**

ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ወላጆች ኑዛዜ ማድረግ አለባቸው:: ልጆቻቸውን የሚንከባከብላቸው ዘመድ፣ ጓደኛ ፣ ሌላ ሰው ማዘጋጀት አለባቸው፣ በራሳቸውና ለሌሎች ሰላምና እፎይታን መፍጠር አለባቸው:: የሚወዷቸውን ሌሎች ሰዎች ከአደጋ ለመጠበቅ የሚያስችሉ ሌሎች ተግባራትንም በህይወት ሳሉ ማከናወን አለባቸው::

እንደነዚህ ያሉ ወላጆች ለልጆቻቸው ስለበሽታቸው እንዲያወሩ፣ ህፃናት ከእነርሱ ስለበሽታው መስማታቸው ጠቃሚ በመሆኑ/ ምክርና ድጋፍ ሊሰጣቸው ይገባል:: ከሁሉም በላይ ህፃናት የወላጆቻቸውን ሞት እንዲረዱና በፀጋ እንዲቀበሉ ተገቢው እገዛና መንፈሳዊ ምክር ያስፈልጋቸዋል::

ተ. **ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር ለሚኖሩ ሰዎች ተገቢውን ህክምና፣ ድጋፍና እንክብካቤ ማድረግ አግባብ የሆነ የሞራል ሃላፊነት ብቻ ሳይሆን ለውጤታማ የመከላከል ስራ ወሳኝ ነው::**

በመላው አለም የተስተዋሉ ተሞክሮዎች እንደሚያሳዩት ተገቢው የድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎት በሌለበት የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ወረርሽኝ ለመግታት የተቻለበት ሁኔታ አልነበረም::

የመከላከል ስራ ውጤታማ የሚሆነው ሰዎች በኤች.አይ.ቪ ወይም ኤድስ ሳቢያ ስራቸውን ወዳጆቻቸውን፣ ቤተሰባቸውን ማህበራዊ ቦታቸውን ወዘተ የማጣት ስጋት ካልደረሰባቸው ብቻ ነው:: ካለፍራቻ የህክምና አገልግሎትና በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የምክርና የምርመራ አገልገሎት ተጠቃሚዎች ሲሆኑ ብቻ ነው::

ቸ. ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ዜጎች ድጋፍና እንክብካቤ እንዲሁም ከመገለልና ሌሎች ጥቃቶች ጥበቃ ማግኘታቸውን እርግጠኛ ሲሆኑ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የመከላከልና መቆጣጠር ዘመቻው ግንባር ቀደም ተዋናይ ይሆናሉ::

## 3.3. **ድጋፍና እንክብካቤ**

## 3.4 ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር በአዎንታዊ መልኩ መኖር ማለት ምንድነው?

- መንፈሳዊና አዕምሯዊ ጤንነትን መጠበቅ

  - ፈጣሪ ጥንካሬን፣ ደህንነትን፣ ሰላምን እንዲሰጣቸው መፀለይ፣
  - የሃይማኖት አባቶችን ክትትልና ምክር መሻት፣
  - ከራስ አገዝ ቡድኖች ጋር አብሮ መስራት፣
  - ስሜትን ከቤተሰቡና ከልጆችና ከሌሎች ባልንጀራዎች ጋር መጋራት፣
  - አዎንታዊ በሆነ መልኩ ማሰብ።

- ጠቃሚ የጤና ምርጫዎችን ማድረግ፤

  - ህመም በተሰማ ጊዜ ሁሉ የህክምና ድጋፍ ማግኘት፣
  - ለጤንነትና ለአካል ጠቃሚ የሆኑ ምግቦችን መመገብ፣
  - በርካታ ውሃ መጠጣት፣
  - ጥሩ የንፅህና አጠባበቅ ልማድን ማዳበር፣
  - ባስፈለገ ጊዜ ተጨማሪ እረፍት ማድረግ፣
  - ማጨስና አልኮል መጠጣትን ማስወገድ።
  - ከኤች.አይ.ቪ ከመጋለጥ በመከላከል የሌሎች ሰዎችን ጤና መጠበቅ።

- አለማዊ ጉዳዮችን በሥርዓቱ ማስተናገድ

  - ከሌሎች ጋር ሰላምን መፍጠር፣
  - ህፃናት እንክብካቤ እንዲያገኙ ማመቻቸት።
  - Making a will

- በተቻለ መጠን መደበኛ የሆነ አኗኗር መኖር
  - አቅም በፈቀደ መጠን ሁሉ የተቻለውን ያህል ስራ መስራት፣
  - ከቤተሰብና ከጓደኞች ጋር አብሮ ማሳለፍ፣
  - በሃይማኖታዊ፣ ሙያዊና ማ/ሰባዊ ተቋማትና አገልግሎቶች ውስጥ ንቁ ተሳታፊ መሆን።

## 3.3.5 ምን ማድረግ እንችላለን

### ሀ. ዝምታውን መስበር

- በተለያዩ መርሃ ግብሮቻችን ወቅት ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩትንና በዚሁ ምክንያት ያለፉትን ማሰብ፤ ብገለፅወያየት

- ከኤችአይቪ/ኤድስ ጋር ከሚኖሩ ግለሰቦችና ቡድኖች ጋር በፍላጎታቸው እንዲሁም ሌሎች መሰሎቻቸው ሊያበረክቱ ከሚችሉት ጥንካሬና መልካም አስተዋፅኦ ዙሪያ መነጋገር።

ለ. ግዴለሽነትን ማብቃት

ኤች.አይ.ቪ. በተራ ንኪኪ እንደማይተላለፍ ማስገንዘብ፣
ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ሰዎች፣ ቤተሰቦቻቸው እንክብካቤ አድራጊዎችና ማ/ሰቡ ምን አይነት መንፈሳዊና አካላዊ አገልግሎትና መረጃ እንደሚፈልጉ መወያየት

ሐ. ፍራቻና ጥላቻን መከላከል

ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ሰዎችን በመጎብኘት፣ መንፈሳዊ አገልግሎትና ምክር በመስጠት፣ ቤተሰቡንና ህመምተኛውን በማበረታታት፣ ፍቅርና ርህራሄን በማሳየት

ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ሰዎች ከሌሎች ጋር እኩል የሆነ ሰብአዊ ክብር እንዳላቸውና ከመገለል ጥበቃ ሊደረግላቸው እንደሚገባ ከተለያዩ አካላት፣ ከቤ/ክ መሪዎችና ምዕመናን፣ እንዲሁም ከህ/ሰቡ ክፍሎች ጋር ውይይት ማድረግ ፡፡

መ. የተለያዩ አገልግሎቶችንና ድጋፎችን ማስተባበር፣ ማጠናከርና ማበረታታት

ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ሰዎችና ቤተሰቦቻቸው እንዲሁም ወላጅ አልባና ሌሎች ተጋላጭ ህፃናት በቂና የተሟላ የማህበረሰብና የቤት ውስጥ እንክብካቤ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ መንፈሳዊና መሰል ድጋፎችን እንዲያገኙ ማድረግ፤ ህ/ሰቡን ማንቀሳቀስ፣ የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን ማበረታታት /ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር ለሚኖሩ ሰዎች እንክብካቤ የሚያደርጉ ወገኖች የተለየ መንፈሳዊ ድጋፍና ማበረታታት እንደሚሹ መገንዘብ ጠቃሚ ነው/

በቤት ውስጥ ለህመምተኛ እንክብካቤ ከማድረግ አንፃር ሴቶችና ልጃገረዶች የተለየ ጫናና ሃላፊነት እንደሚጣልባቸው በዚህም ሳቢያ ከትምህርት መሰል ማህበራዊ አገልግሎቶች እንደሚርቁና አካላዊና አዕምሯዊ ተፅዕኖ እንደሚያድርባቸው በመረዳ እንደነዚህ ያሉ ሴቶችና ልጃገረዶች የተለየ ድጋ የሚያገኙበትን መንገድ መፈለግ፣ ወንድ አዋቂዎችና ወጣቶችመ ህመምተኞችን ከመንከባከብ አንፃር ትልቁን ሃላፊነት እንዲሸከሙና እንዲጋሩ ማበረታታት፤

ሠ. ማህበራዊ እሴቶችንና ፖሊሲዎችን ማጠናከር

አግባብ የሆኑ ፕሮግራሞችንና አገልግሎቶችን በማቀድና መተግበር ሂደት ውስጥ ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ሰዎች ተሳትፎ እንዲጠናከር ማድረግ፤

ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ሰዎችና ነፍሰጡር ሴቶች የAntiretroviral ህክምና አገልገሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን መደገፍ፤

ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ሰዎችና ቤተሰቦቻቸውን የንብረትና የመሬት ባለቤትነት፣ የመስራት፣ የመንቀሳቀስ፣ ከማህበራዊ አገልግሎቶች እኩል የመጠቀምና የመሳተፍ . ወዘተ መብቶች እንዲከበሩ ማድረግ፤ ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ሰዎች በአግባቡ/አዎንታዊ በሆነ መንገድ /እንዲኖሩ ማበረታታት፤

# 4. ሴቶችና ልጃገረዶች

- የተለያዩ አይነት ሴቶችና ልጃገረዶች እንደመኖራቸው በዚህ ፅሁፍ በተለይ ትኩረት የተሰጣቸው

  - በትዳር አለምና በቤተሰብ ደረጃ ያሉ፣
  - በጉሊት በአነስተኛ የአልኮልና ሌሎች ሸቀጦች ንግድ የተሰማሩ፣
  - በቡና ቤት ህይወት ውስጥ የሚገኙ፣
  - በት/ቤትና ከት/ቤት ውጪ ያሉና ወጣት የሆኑ፣
  - በሰው ቤት ተቀጥረው እየሰሩ ያሉ፣
  - ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ እና የመሳሰሉ ሴቶችና ልጃገረዶች ናቸው::

## 4.1. <u>እውነታው</u>

በተለይ በታዳጊ አገራት የሚገኙ ሴቶች ከወንዶች በበለጠ ሁኔታ የድህነት ተጠቂ ናቸው:: በድህነት ሳቢያ የሚፈጠሩ ተፅዕኖዎችና ጫናዎች ከማንም በላይ በሴቶች ላይ የበረታ ነው::
አገራችንን ጨምሮ በበርካታ የአፍሪካ አገራት ተንሰራፍቶ በሚገኘው የስርዓተ ፆታ መዛባት /የፆታ ተፅዕኖ/ ሳቢያ ሴቶች ለበርካታ ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ስነልቦናዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋልጠው ይገኛሉ::

አሁን ደግሞ በተለይ ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ አገራት የኤች.አይ.ቪ ስርጭት ከወንዶች ይልቅ በሴቶች ላይ የበዛ ነው:: እ.ኤ.አ. በ2003 መረጃ መሰረት እድሚያቸው ከ15 - 49 የሆኑና ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ የደቡብ ሰሃራ አፍሪካ አገራት የሴቶች ቁጥር 13.1 ሚሊዮን ሲገመት የወንዶቹ ደግሞ 9.9 ሚሊዮን ነበር:: ስርጭቱ በተለይም ከ15 - 24 ዓመት እድሜ ውስጥ ባሉ ወጣት ሴቶች ላይ አይሎ ይታያል:: በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሳቢያ የሚመጡ በርካታ ተፅዕኖዎችም በአብዛኛው ከወንዶች ይልቅ በሴቶች ላይ አስከፊ ጫናዎችን እያስከተሉ ናቸው::

<u>ምንጭ:</u>
" Women & HIV/AIDS confront the crisis"
A Joint report UNAIDS/UNFPA/UNIFEM (UN don't found for women)

- ይህ አይነቱ አስደንጋጭ እውነታ ባለበት ሁኔታ ውስጥ ሴቶች ስለኤች.አይ.ቪ መተላለፊያና መከላከያ መንገዶች ያላቸው ግንዛቤ ከወንዶች ያነሰ ነው:: ሴቶች ያላቸው መጠነኛ እውቀትም ብትሆን ተንሰራፍቶ ባለው የመድልዎና የፆታ ጥቃት ሳቢያ ራሳቸውን ለመከላከል ጥቅም ላይ መዋል አልቻለችም::

- የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ስርጭትና የሚያስከትላቸውን አሉታዊ ተፅዕኖዎች በብቃት መከላከል የሚቻለው ደግሞ በሴቶች ላይ ለሚደርሱ ሶስትዮሽ ችግሮች ድህነት፣ የሥርዓተ ፆታ መድሎና፣ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ተፅዕኖዎች በአግባብነት ያለው የተጠናከረ ምላሽ ስንሰጥ ብቻ ነው::

- ሴቶች የአደጋ ሰለባዎች ብቻ ተደርገው መታየት የለበትም ኤች.አይ.ቪ/ኤድስንና ድህነትን በመዋጋቱ ረገድ ሴቶች ግንባር ቀደምና ውጤታማ ሚና መጫወት

እንደሚችሉ መታመን አለበት፡፡ በአለማችን ባሉ የተለያዩ ማ/ሰቦች ውስጥ ሴቶችና ወንዶች የህ/ሰቡን ግንዛቤ በማዳበር የፆታና የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶችና ትምህርቶችን በማስፋፋት ሴቶች እራሳቸውን ከኤች.አይ.ቪ. የሚከላከሉባቸውን ክህሎቶችን በማስጨበጥ የስርዓተ ፆታ መድሎንና የፆታ ጥቃትን በመታገልና በመሳሰሉት ረገድ በርካታ ውጤታማ እርምጃዎችን ወስደዋል፡፡

- እ.ኤ.አ በ2003 መረጃ መሰረት በዓለማችን 17 ሚሊዮን ሴቶችና 18.7 ሚሊዮን ወንዶች /ከ15-49 እድሜ/ ከኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ጋር አብረው ይኖራሉ፡፡ 1985 /እ.ኤ.አ/ ወዲህ ብቻ በአለማችን ከኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ጋር የሚኖሩ ሴቶች አሃዝ ከ35 በመቶ ወደ 48 በመቶ አድጓል ፡፡

- በተለይ እስደንጋጭ የሆነው ሁኔታ ደግሞ እድሜያቸው ከ15-24 አመት በሚሆናቸው ወጣት ሴቶች ላይ እየጨመረ የመጣው የኤች.አይ.ቪ. ስርጭት ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት እድሜያቸው 15-24 አመት ክልል ውስጥ ከሚገኙና ከኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ጋር የሚኖሩ ወጣቶች መካከል የሴቶች መጠን 60 በመቶ ያህል ነው፡፡
- በአለም አቀፍ ደረጃ ወጣት ሴቶች ከኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ጋር የመኖር እድላቸው ከወጣት ወንዶች ጋር ሲነፃፀር በ1.6 ጊዜ ይበልጣል፡፡

- በአለማችን ከሚገኙ ከኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ጋር ከሚኖሩ ሰዎች ውስጥ 98 በመቶ ሴቶችና 94 በመቶ ወንዶች በታዳጊ አገራት የሚገኙ ሲሆን 77 በመቶ ሴቶች የሚኖሩት ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ አገራት ነው፡፡